በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# አሠርቱ ትእዛዛት - ክፍል ፬

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com

***<u>ቦታ፡-</u>*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

መጋቢት ፳፩ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - ሦስተኛው ትእዛዝ</u>

- ‹‹የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፡፡ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው አንተ፥ ወንድ ልጅህም፥ ሴት ልጅህም፥ ሎሌህም፥ ገረድህም፥ ከብትህም፥ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ። እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፥ ባሕርንም፥ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም።» ***<u>ዘጸ 20፡8-11፡፡</u>***

***<u>«የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ።</u>***»

- ይህ ትእዛዝ አሠርቱ ትእዛዛት ከመሰጠታቸው አስቀድሞ እስራኤል ይጠቀሙበት ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠው ቀዳማዊ ትእዛዝ ነው፡፡
- «እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ። እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ ዐርፎአልና።» ***<u>ዘፍጥ 2፡2-3፡፡</u>***
- እግዚአብሔር ፍጥረታትን ከፈጠረባቸው ዕለታት ሁሉ ይልቅ በተለየ ክብር የሰንበትን ቀን ባርኮታል፡፡ ቀድሶታልም፡፡ ሌሎቹን ዕለታት ሠርቶባቸው ለሥራ ባርኮ ሰጥቶናል፡፡

***<u>ሰንበትን የማክበር ትእዛዝ መቼ ተጀመረ?</u>***

- አሠርቱን ትእዛዛት ከመስጠቱ አስቀድሞ «እርሱም፡- እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው። ነገ ዕረፍት፥ ለእግዚአብሔርም የተቀደሰ ሰንበት ነው የምትጋግሩትን ጋግሩ፥ የምትቀቅሉትንም ቀቅሉ፥ የተረፈውን ሁሉ ለነገ እንዲጠበቅ አኑሩት አላቸው። … ሕዝቡም በሰባተኛው ቀን ዐረፈ።» ***<u>ዘጸ 16፡23-30</u>*** እንደተገለጸው ሰንበትን ማክበር ይታወቅ ነበር፡፡

# አሠርቱ ትእዛዛት - ሦስተኛው ትእዛዝ

***ሰንበትን አለማክበርና የሚያስከትለው ቅጣት***

- «ስድስት ቀን ሥራን ሥራ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ የዕረፍት ሰንበት ነው በሰንበት ቀን የሚሠራ ሁሉ ፈጽሞ ይገደል።» ***ዘጸ 31፡15፡፡***
- ሰንበትን መሻር ከባድ ኃጢአት ነበር፡፡ ሰንበተን በመሻሩ የተነሳ የተቀጣ አንድ ሰው ታሪክም ***በዘኊ 15፡32-36*** ይገኛል፡፡
- ነቢዩ ሕዝቅኤልም ይህንኑ አስመልክቶ በትንቢት መጽሐፉ «ልጆች ግን ዐመፁብኝ፥ ሰው ቢያደርገው ኖሮ በሕይወት የሚኖርባትን ፍርዴን ጠብቀው አላደረጓትም በሥርዓቴም አልሄዱም፥ ሰንበታቴንም አረከሱ በዚህም ጊዜ። መዓቴን አፈስስባቸዋለሁ ቍጣዬንም በምድረ በዳ እፈጽምባቸዋለሁ አልሁ።» ***ሕዝ 20፡21*** በማለት እግዚአብሔር የተናገረውን ጽፎልናል፡፡

***ሰንበት የተሠራችው ለሰው ነው፡፡***

- አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሰንበት ለሰው ተፈጥሮአል እንጂ ሰው ስለሰንበት አልተፈጠረም፡፡» ***ማር 2፡27*** በማለት የነገረን ሰንበት ለሰው ጥቅም የተፈጠረች መሆንዋን ያመለክታል፡፡
- በሰንበት ሰው ሁሉ፣ እንስሳትም፣ መሬትም ሁሉ ማረፍ ይኖርባቸዋል፡፡ «ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር አምላክህ ሰንበት ነው አንተ እንደምታርፍ ሎሌህና ገረድህ ያርፉ ዘንድ፥ አንተ ወንድ ልጅህም ሴት ልጅህም ሎሌህም ገረድህም በሬህም አህያህም ከብትህም ሁሉ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ። አንተም በግብፅ ባሪያ እንደ ነበርህ አስብ እግዚአብሔር አምላክህ በጸናች እጅና በተዘረጋ ክንድ ከዚያ አወጣህ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ የሰንበትን ቀን ትጠብቅ ዘንድ አዘዘህ።» ***ዘዳግ 5፡14-15፡፡***

# አሠርቱ ትእዛዛት - ሦስተኛው ትእዛዝ

***ሰንበት የተሠራችው ለሰው ነው…***

- «ስድስት ዓመት ምድርህን ዝራ፥ ፍሬዋንም አግባ በሰባተኛው ዓመት ግን ተዋት አሳርፋትም የሕዝብህም ድሆች ይበሉታል ያስቀሩትንም የሜዳ እንስሳ ይብላው። እንዲሁም በወይንህና በወይራህ አድርግ። ስድስት ቀን ሥራህን ሥራ በሬህና አህያህ ያርፉ ዘንድ ለባሪያህም ልጅ ለመጻተኛውም ዕረፍት ይሆን ዘንድ በሰባተኛው ቀን ዕረፍ።» ***ዘጸ 23፡10-12፡፡***
- ሰንበትን ብናከብር «ሰንበቴን የሚጠብቁትን፣ ቃል ኪዳኔንም የሚይዙትን ሁሉ ወደ ተቀደሰው ተራራዬ አመጣቸዋለሁ፤ በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ፤… የማይጠፋ የዘላለምም ስም እሰጣቸዋለሁ፡፡» ***ኢሳ 56፡2-7*** በማለት የሚያስገኘውን በረከት በመግለጽ እግዚአብሔር ቃል ገብቶልናል፡፡

***ሰንበት የዘላለማዊ ዕረፍት ምሳሌ ናት፡፡***

- «ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው። እኔ የምቀድሳችሁ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቁ ዘንድ በእኔና በእናንተ ዘንድ ለልጅ ልጃችሁ ምልክት ነውና ሰንበቶቼን ፈጽሞ ጠብቁ።» ***ዘጸ 31፡13፡፡*** እንዳለን ሰንበት የዘላለማዊው ዕረፍት ምልክት ሆና ተሰጥታናለች፡፡
- በብሉይ የነበረው የሰንበት ዕረፍት ለሥጋ ነበር እርሱም በሐዲስ በክርስቶስ ትንሣኤ በሰንበተ ክርስቲያን ተተርጉሟል፡፡

***በሰንበት ምንም ምን የሥጋ ሥራ አይሰራም፡፡***

- በሰንበት በጎ ከማድረግ ውጪ ዘወትር የሚሠሩትን የሥጋ ሥራ መሥራት አልተፈቀደም፡፡ ***ዮሐ 5፡2-11፣ ሉቃ 14፡1-6 ፣ ማቴ 12፡10-13፣ ሉቃ 13፡10-16፣ ዮሐ 9፡14…*** «ከእናንተ አንድ በግ ያለው በሰንበት በጉድጓድ ቢወድቅበት፥ ይዞ የማያወጣው ሰው ማን ነው? እንግዲህ ሰው ከበግ ይልቅ እንደምን አይበልጥም! ስለዚህ በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዶአል አላቸው።» ***ማቴ 12፡11-12፡፡***
- ሰንበት ለመንፈሳዊ ሥራ እንዲውል መታዘዙ ***ዘሌ 23፡3***፣ የአምልኮት መፈጸሚያነቱም ***ኢሳ 66፡23***፣ ሐዋርያት ያስተማሩበት ዕለት መሆኑም ***ማር 6፡2፣ የሐዋ 18፡4፣ የሐዋ 17፡1-2*** ተጽፈው ይገኛሉ፡፡

# አሠርቱ ትእዛዛት - ሦስተኛው ትእዛዝ

***ቅዳሜና እሁድ - ሰንበት***

- የቅዳሜ መከበር በብሉይ የታዘዘ ሲሆን የክርስቲያኖች ሰንበት አከባበር ግን በፍትሐ ነገሥት «ለክርስቲያን እንደ አይሁድ ዕለተ ሰንበትን ማክበር አይገባም፤ ለክርስቲያን እንደ ሚገባ በመንፈሳዊ ሥራ በመትጋት ነው እንጂ፡፡» እንደተባለው ነው፡፡
- እሁድ ጌታ ከሙታን ተለይቶ የተነሳባት ***ራእ 1፡10***፣ ዳግመኛ ለፍርድ ስለሚመጣባት ***ዘካ 14፡4***፣ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ስለወረደባት ***የሐዋ 2፡1 እና የሐዋ 20፡7***፣ ቅዱስ ጳውሎስም ይህችን ዕለት እየጠቀሰ በመጻፉ ***ቀዳ ቆሮ 16፡1-4***፣ ልበ አምላክ ዳዊትም በመዝሙሩ «የእግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት፤ ሐሴትም እናድርግ በእርስዋም ደስ ይበለን፡፡» ስለዘመረላት ***መዝ 117፡24*** ክርስቲያኖች እናከብራታለን፡፡ ቀድሞም ቢሆን ሕዝበ እስራኤል ቀዳምያቱንና በኩራቱን የሚያስረክቡበት ዕለት እሁድ ነበረች፡፡ ***ዘሌዋ 23፡9-16፡፡***
- በመሆኑም በምስጋና (ቅዳሴ፣ ማኅሌት፣ ሰዓታት፣ መዝሙር…)፣ መንፈሳዊ ትምህርቶችን በመማር፣ በጎ ሥራዎችን በመሥራት የክርስቲያኖች ሰንበት እሁድንም እናከብራለን፡፡
- ሰንበትን ድኾችን የታመሙትንና የታሰሩትን በመጠየቅ፣ የተራቡትን በማብላት፣ የተጠሙትን በማጠጣት፣ የታረዙትን በማልበስ ክርስቲያኖች ሁሉ ሊያከብሩ እንደሚገባ ለማስረዳት «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ» የሚል ትእዛዝ ሰጥቶናልና ሰንበት አይሁድ (ቅዳሜንና) ሰንበተ ክርስቲያን (እሁድን) እናክብር፡፡

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - አራተኛው ትእዛዝ</u>

- ‹‹አባትህንና እናትህን አክብር እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም።» <u>*ዘጸ 20፡12፡፡*</u>

<u>*‹‹አባትህንና እናትህን አክብር።»*</u>

- ይህ ትእዛዝ በሰዎች መካከል የሚኖረውን ግኑኝነት አስመልክቶ የተሰጠ የመጀመሪያ ትእዛዝ ነው፡፡ እስከሁን የተመለከትናቸው ሦስቱ ትእዛዛት ሰው ለእግዚአብሔር ሊያደርገው የሚገባውን ሲያመለክቱ ይኽኛው እና ተከትለውም የሚገኙ ትእዛዛት ግን ሰው ለሰው ሊያደርገው የሚገባውን ይመለከታሉ፡፡
- በዚህ ትእዛዝ ትእዛዙን በመጠበቅ የሚገኘውም በረከት አብሮ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡
- እናቱንና አባቱን የሚያከብር እግዚአብሔር በሚሰጠው ምድር ዕድሜው ይረዝማል፣ መልካምም ይሆንለታል፡፡ <u>*ዘዳግ 5፡16፡፡*</u> ቅዱስ ጳውሎስም «መልካምም እንዲሆንልህ፣ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትና እናትህን አክብር፤ እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት፡፡» በማለት የጻፈልን ይህ ትእዛዝ ከሌሎቹ ተለይቶ ትእዛዙን በመጠበቅ የሚገኘው በረከት የተገለጠበት ትእዛዝ ስለሆነ ነው፡፡ <u>*ኤፌ 6፡2-3፡፡*</u>

<u>*ወላጆችን ማክበር እንዴት ነው?*</u>

1. <u>*በማፍቀር*</u>

- ልጅ አስቀድሞ የሚያውቀው የእናቱንና የአባቱን ፍቅር ስለሆነ በሚቻለው ሁሉ መጠን ለወላጆቹ ያለውን ፍቅር በምግባር መግለጥ ይጠበቅበታል፡፡
- ወላጆቹን ከልብ የሚወድድ ልጅ ቃላቸውን ያከብራል፣ የሚሉትንም በጎ ነገር ይፈጽማል፡፡ ስለዚህ ወላጆችን መውደድ አንዱ የፍቅር መግለጫ መንገድ ነው፡፡

# አሠርቱ ትእዛዛት - አራተኛው ትእዛዝ

***ወላጆችን ማክበር እንዴት ነው?***

2. ***በፈቃደኝነት በመታዘዝ***

- ጌታችን ለእናቱ ለእመቤታችንና ለጠባቂዋ ለዮሴፍ ይታዘዛቸው ነበር፡፡ ***ሉቃ 2፡51፡፡***
- ይስሐቅ ለአባቱ ለአብርሃም ያሳየው ታዛዥነትም ታላቅ ትምህርት ነው፡፡ ***ዘፍጥ 22፡1-14፡፡***
- ፈቃደኝነትና ታዛዥነት የትሕትና፣ የመንፈስ ፍሬዎችና ራስንም ዝቅ የማድረግ ውጤቶች ናቸው፡፡ በእነዚህም አማካኝነት ወላጆችን ማክበር ያስፈልጋል፡፡

3. ***በመርዳት***

- ልጅ ወላጆቹ እርዳታውን በሚፈልጉበት ጊዜ አቅሙ በፈቀደ መጠን የመርዳት ግዴታ አለበት፡፡
- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ነገር ግን ለእርሱ ስለሆኑት ይልቁኑ ስለ ቤተሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖቱን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የከፋ ነው፡፡» ***ቀዳ ጢሞ 5፡8፡፡*** በማለት የጻፈልን ይህንኑ አስመልክቶ ነው፡፡
- ጻድቁ ዮሴፍ አባቱ ያዕቆብን ይረዳው እንደነበር ***ዘፍጥ 45፡9-11*** ተጽፎልናል፡፡
- ስለዚህ ወላጆችን መርዳት አክብሮትን መግለጫ አንዱ መንገድ መሆኑን እንገንዘብ፡፡

4. ***መልካም ፍሬ በማፍራትና ጥሩ ውጤት በማምጣት***

- በመጽሐፍ ቅዱስ «ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል፣ ሰነፍ ልጅ ግን ለእናቱ ሐዘን ነው፡፡» ***ምሳ 10፡1***፣ እንዲሁም «የጻድቅ አባት ደስ ይለዋል ጠቢብንም ልጅ የወለደ ሐሴትን ያገኛል፡፡» ***ምሳ 23፡24፡፡*** በማለት ጠቢቡ ሰሎሞን የጻፈልን መልካም ፍሬ እያፈሩ፣ በሥራም ውጤታማ እየሆኑ ወላጆችን ማስደሰት የማክበር አንዱ ገጽታ ስለሆነ ነው፡፡

5. ***ወላጆች ያደረጉልንን በማሰብ***

- ወላጆች ከጽንስ እስከ ጉልምስና ያደረጉትን በማሰብ ፍቅራቸውን ማስታወስ ይገባል፡፡
- አባትና እናት የሚለው ክብር የሚመለከታቸው ሌሎቹ መንፈሳውያን አባቶችና እናቶች፣ አረጋውያን፣ … ናቸው፡፡
- ከሁሉ በፊት መታዘዝ ለእግዚአብሔር ሲሆን ከአምላካችን ፈቃድ ለሚጣላ ነገር እግዚአብሔርን እንዳናሳዝን መጠንቀቅ ይገባል፡፡ ***ኤፌ 6፡1***፡፡

# አሥርቱ ትእዛዛት - አራተኛው ትእዛዝ

***አባትና እናትን አለማክበር ያስቀጣል፡፡***

- በብሉይ አባትንና እናትን አለማክበር በሞት ያስቀጣ ነበር፡፡ ***ዘጸ 21፡15-17፣ ዘሌዋ 20፡9፡፡***
- ጌታችን አምላካችን ፈሪሳውያንን በገሠጸበት ክፍል አባትና እናትን ማክበር እንደሚገባ ሲገልጥ «ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል። ሙሴ። አባትህንና እናትህን አክብር፤ ደግሞ። አባቱን ወይም እናቱን የሰደበ ፈጽሞ ይሙት ብሎአልና። እናንተ ግን ትላላችሁ። ሰው አባቱን ወይም እናቱን። ከእኔ የምትጠቀምበት ነገር ሁሉ ቍርባን ማለት መባ ነው ቢል፥ ለአባቱና ለእናቱ ምንም እንኳ ሊያደርግ ወደ ፊት አትፈቅዱለትም፤ ባስተላለፋችሁትም ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ፤ እንደዚሁም ይህን የሚመስል ብዙ ነገር ታደርጋላችሁ።» ***ማር 7፡9-13፡፡*** ብሎአል፡፡
- አባትና እናቱን የሚሰድብ እርግማን ይከተለዋል፡፡ «እናቱን ወይም አባቱን የሰደበ በድቅድቅ ጨለማ መብራቱ ይጠፋል፡፡» ***ምሳ 20፡20፣ ዘዳ 27፡16***፣ «በአባትዋ የምታላግጥን የእናትዋን ትእዛዝ የምትንቅን ዓይን የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጉቱአታል አሞራቆችም ይበሉአታል፡፡» ***ምሳ 30፡17፣ ዘፍ 9፡20::***
- አባት የቤተሰብ ራስና አስተዳዳሪ ቤተሰቡንም ከእግዚአብሔርም ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡ አብርሃም፣ ያዕቆብ ይስሐቅ ሥራቸው ይኸው ነበር፡፡ ከወላጆቹ በረከትን የተቀበለ ከእግዚአብሔርም ይቀበላል፡፡
- ስለዚህ ዕድሜአችን እንዲረዝም መልካምም እንዲሆንልን አባቶቻችንንና እናቶቻችንን እናክብር፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org

ይቆየን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡